- 8 -

ልብህን አስመልስ

ማንም መውደቅን (መሸነፍን) አይፈልግም። መስጠምንም የሚመርጥ የለም። ግና በዚህ ውቅያኖስ በሆነ ዓለም ዱንያ ወደ ውስጣችን ሰርጋ እንዳትገባ ለማድረግ ትግሉ ከባድ ነው። አንዳንዴ ውቅያኖሱ ወደ ውስጣችን ይሰርጋል። አንዳንዴ ይህች ዓለም ወደ ልባችን ትሰርግለች። ዱንያ ወደ ልባችን ውስጥ ዘልቃ መግባት የሌለባት ውቅያኖስ ናት። ከገባች ሚዛናችን አስታ ታሰጥመናለች።

የባህሩ ውሃ ወደ መርከቢቱ ሲገባ እንደሚሰብራት ሁሉ ዱንያ ወደ ቀልባችን ከገባች ሰብራ ትጥለናለች። የተሰበረ መርከብ ምን እንደሚመስል በቅርቡ የሆነውን አስታወስኩ። ይህም ሁሉንም ነገር ወደ ውስጣችን እንዲዘልቅ ስንፈቅድ የሚከሠተው ነው። ይህንን የማስታውሰውም - አንዲት ወዳጄን በማየቴ ነው - ልክ እንደ እኔ በዚህች ዓለም ሕይወት ፍቅር ተጠልፋ የምትባክን፣ በፍጥረታት መከበብን ምርጫዋ ያደረገች ነበረች...። እና ዱንያ በውስጧ ስትዘልቅ ሰብራ ጣለቻት። ልክ የኔን መርከብ እንደሰበረችው ሁሉ የርሷንም መርከብ ሰብራ ጣለች። እናም ከውሃው ለመውጣት ሞከረች። ግና ከዚያ መዓት እንዴት መውጣት እንደምትችል ሳታውቅ ረጅም ጊዜ እዚያው ውስጥ ቆየች። በዚያውም ሰጥማ ቀረች!!

ውቅያኖሱ መርከቢቱን እንደተቆጣጠረው ሁሉ ዱንያ ልባችንን እንድትቆጣጠር ከፈቀድን ሁሉም ነገር ያበቃለታል። ወደ ባህሩ ወለል እንዘቅጣለን። ያኔ እጅግ ዝቅተኛ ወደ ሆነው ቦታ እንወርዳለን። ይህ የሆነው በወንጀላችን እና በዚህ ዓለም ፍቅር በመጠመዳችን ምክንያት ነው። በዚህም የተነሳ ዙርያችንን በጨለማ የተከበብን የተሰበርን ሆነን ይሰማናል። ስለባህሩ የታችኛው ወለል ስናስብ አስደናቂው ነገር አለው። እሱም ምንም ብርሃን ነገር የሚባል የማይደርስበት ቦታ መሆኑ ነው። በዱንያ ጨለማ ስንዋጥም እንደዚያው ነው።

እንዲህ በዘቀጣችሁ ጊዜ አንድ ነገር አስታውሱ፤ ግና ይህ የጨለማ ክፍል መጨረሻው አይደለም። ልክ ከንጋት በፊት ያለው ጨለማ እንደሆነው ሁሉ ልባችሁ መምታቱን እስካላቆመ ድረስ ይህ መጨረሻችሁና ሞታችሁ ሊሆን አይችልም። እዚህ ቦታ ላይ አትሞቱም። አንዳንዴ፤ የባህሩ ወለል ከባሰው መጥፎ መንገዳችሁ የሚያቆማችሁ ብቻ ነው የሚሆነው። የባህሩ ወለል ማብቂያ መጨረሻው ብቻ ሳይሆን ከምርጫዎቻችሁ ጋር ፊት ለፊት የምትገናኙበትም ጭምር ሊሆን ይችላል። በባህሩ ወለል ላይ በምትቆዩበት ጊዜም የምታተርፉት ነገር ይኖራል። ምናልባትም እንደገና ኃይላችሁን አሰባስባችሁ ውድ ጌጣጌጦችን ጭምር ሰብስባችሁ ከዘቀጣችሁበት ወለል ከፍ ልትሉ ትችላላችሁ።

አላህ (ሱ.ወ.) ከሻላችሁ እሱ ራሱ ያነሳችኋል፤ የባህሩን ጨለማም በራሱ የፀሐይ ብርሃን ይተካላችኋል። ባንድ ወቅት ትልቁ ድከመታችሁ የነበረውን ጎን በላቀ ጥንካሬ

ይለውጠዋል። ለማደግም ምክንያት ይሆናችኋል። እናም የምትጠሩበትና ከፍ የምትሉበት ሰበብ ያደርግላችኋል። እመኑ...አንዳንዴ ጊዜ ምርጥ የሆነ ለውጥ የሚመጣው ከውድቀት በኋላ መሆኑን እንድታውቁ። ስለሆነም ውድቀታችሁን አትርገሙ። መውደቃችሁን አትጥሉ። ወደ ባህሩ ወለል መውደቃችሁ ለመነሳታችሁ መሰረት ነው የሚሆነው። እናም ውድቀትን ተቀበሉ፤ ተማሩበት። ወደ ውስጣችሁ ኃይላችሁን አሰባስቡና ጠንካራ ሆናችሁ ተነሱ። ትሁትና በይበልጥ እሱን ፈላጊ ሆናችሁ ውጡ። ዳግም ስትነሱ እናንተ ምንም እንዳልሆናችሁ እና የሱን ታላቅነት ትረዳላችሁ። ያንን እውነታ መመልከት ከቻላችሁ ሁሉንም ነገር መመልከት ትችላላችሁ። ራሱን የሚያታልል ሰው የራሱን ምስል እንጂ እሱን ፈፅሞ ሊመለከት አይችልም። ያልታደለ ማለት ከአምላኩ ፈላጊ እንደሆነ በራሱ ላይ መመስከር ያልቻለ ሰው ነው። በራሱ ላይ ጥገኛ የሆነ ሰው ነው። መገልገያዎች፣ እሱ ራሱ እና ሁሉም ነገር የአምላክ ተፈጥሮ መሆናቸውን የረሳ ነው።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲያነቃችሁ ከሱ ፈልጉ። እሱ ባሻው ጊዜ የወደመውን ጀልባችሁን ይጠግንላችኋል። ለዘላለሙ ተሰብሮ የቀረ የሚመስላችሁን ልባችሁም ዳግም ሽረትን ያገኛል። ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ የሆነን ነገር እሱ ብቻ ነው መጠገን የሚችለው። ስለሆነም ከርሱ መሻትን ልመዱ።

እርሱ ባዳናችሁም ጊዜ ለውድቀታችሁ የርሱን ምህረት ለምኑ። ፀፀት ይሰማችሁ እንጂ ተስፋ አትቁረጡ። ኢብኑል ቀዪም አላህ ይዘንላቸውና እንዳሉት "አደም (ዐ.ሰ.) ከጀነት በወጡ ጊዜ ሰይጣን ተደስቶ ነበር። ነገር ግን አንድ ያላወቀው ነገር ቢኖር የባህር ጠላቂ ወደ ባህሩ በሰጠመ ጊዜ የከበሩ ማዕድናትና እንቁዎችን እንደሚሰበስብና ዳግም የሚያንሰራራ መሆኑን ነው።"

ይህም ስለ ተውባ (ተፀፅቶ መመለስ) ገራሚውና አስደናቂው ጉዳይ ነው- ወደ ጌታችን የመመለስ ዕድል። እንደተነገረንና እንደተማርነውተውባ ለልባችን ዳግም ንፅህናን ያጎናፅፈዋል። የተውባ ንፅህና አስደናቂው ነገር ልብን ንፁህ ማድረግ ብቻ አይደለም። ከመጨቅየቱ በፊት ከነበረው በበለጠ ሁኔታ ልብን አብረቅራቂ ያደርጋታል። ወደ ጌታችሁ ተመልሣችሁ፤ ማርታውን የሻችሁ እንደሆነ ሕይወታችሁንና ሙሉ ትኩረታችሁን በርሱ ላይ ስታደርጉ ፈፅሞ ልትወድቁ በማትችሉበት ሁኔታ ባለፀጋ የመሆን አቅም ላይ ትሆናላችሁ። ወድቆ በመነሳት ውስጥ ጥበብንና ትህትናን ትማራላችሁ።

ኢብኑል ቀዩም አላህ ይዘንላቸው እንደፃፉት "ከሰለፎች አንዱ እንዳለው አንዱ ኃጢአት ሠራና ጀነት ገባ። ሌላኛው መልካም ሥራ ሠራና ጀሀነም ገባ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ተብሎ ሲጠየቅ ኃጢአት የሰራው ሰውዬ ያለማቁዋረጥ ስለ ኃጢአቱ ነበር የሚያስበው። ይህም ሁሌ እንዲፈራ፣ እንዲፀፀት፣ እንዲያነባ አድርጎት ነበር።፣ በዚህም የተነሳ ጌታው ፊት ለመቆም ሁሉ ያፍር ነበር። ጌታው ፊት ሲቆም በተሰበረ ልብ፣ አንገቱን በመስበርና በመተናነስ ነበር። ስለዚህ ይህ ወንጀሉ ከሠራው ማንኛውም መልካም ነገር በላይ ለሱ

ጠቃሚ ሆኖ ተገኘ። በጌታው ፊት እንዲተናነስና እንዲሰበር አድርጎታልና። ይህም ስኬትና ደስታን አጎናፀፈው። ኃጢአቱ ጀነት እንዲገባ ምክንያት ሆነው። በሌላ መልኩ በመልካም ሥራ ላይ የነበረው የሱ መልካም ሥራ የጌታው ችሮታ መሆኑን ዘንግቷል። በኩራትና እብሪት የተሞላ፣ በራሱ የሚደነቅ ነበር። ይህን ይህን አሳካሁ በማለት ይመፃደቅ ነበር። ይህም ከጊዜ ወደጊዜ ኩራትና ትእቢትን ጨመረለት። ለመጥፊያውም ምክንያት ሆነ። ይህ ነበር ጀሀነም የመግባቱ ምክንያት።

አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአኑ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብን ያስታውሰናል፦

﴿ قُلْ يَٰعِبَادِيَ ٱلَّذِينَ أَسْرَفُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا۟ مِن رَّحْمَةِ ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَغْفِرُ ٱلذُّنُوبَ جَمِيعًا ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴾

"በላችው፥ እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፣ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሃሪው አዛኙ ነውና።" (አዝ-ዙመር ፡ 53)

ይህ ጥሪ ተስፋ ቆርጠው ራሳቸውን እስር ቤት ለከተቱት የፍላጎታቸው ባሮች ለሆኑት የቀረበ ጥሪ ነው። ይህ ጥሪ ወደ ዱንያ ባህር ለገቡና በጥልቀትም ውስጧ ለሰጠሙና በማዕበሏ ለሚንገላቱት ሁሉ የቀረበ ነው። ውጡ! ውጡ! ወደ አየር ውጡ! ... የሚል ጥሪ። ከባህሩ በላይ ወዳለው እውነተኛው ዓለም፣ ወደ እውነተኛው ነፃነታችሁውጡ! ውጡና ነፍስ ዝሩ!. . . የሚል ጥሪ ነው። የነፍሳችሁን ሞት እርሱ። ልባችሁ አሁንም ህያውና ከቀድሞው በተሻለ ጠንካራና ንፁህ ናት ውጡ!።

የተውባ ኃያልነት ልቦናን ንፁህና ከቀድሞው በተሻለ ውብ ሊያደርጋትምን? ያሰጠማችሁን ወንጀል አስወግዱ፤ በናንተና በሕይወታችሁ መካከል ያለውን ግርዶ አንሱ፣ በናንተና በነፃነታችሁ፣ በናንተና በአላህ ብርሃን መካከል የተጋረደውን ግርዶ ግፈፉ። ግርዶአችሁን ግለጡና ዳግም አንሰራሩ። ወደራሳችሁና ወደ መነሻችሁ ተመለሱ። ወደ እውነተኛው ቤታችሁ ተመለሱ። ሁሉም በሮች ቢዘጉ እንኳ ሁሌም ክፍት የሆነ በር አለ። ሁሌም ያንን በር ፈልጉ። እሱን ፈልጉ። በአስፈሪው የባህር ማዕበል መካከል ፀሐዩ ወደሆነው እዝነቱ ይመራችኋልና።

ይህች ዓለም እናንተው ፈቃድ እስካልሰጣችኋት ድረስ አትሰብራችሁም። የልቦናችሁን ቁልፍ እስካላቀበላችኋት ድረስ ልትገዛችሁና የራስዋ ልታደርጋችሁ አትችልም። ለጊዜው እንኳን ቁልፎቹን የሠጣችኋት ቢሆን እንኳን መልሳችሁ ተቀበሉ። ይህ መጨረሻችሁ አይደለም። እዚህ ጋም መሞት የለባችሁም። ልባችሁን አስመልሱና ለትክክለኛው ባለቤቱ አስረክቡ።

እሱ አላህ ነው።

ምዕራፍ ሁለት - ፍቅር

- 9 -

ከአደገኛው እስር ቤት ማምለጥ

ሳራ አሕመድን ስታገኘው ወዲያውኑ አንድ ነገር ትረዳለች። እሱ ማለት እሷ ሁሌ የምታልመው ሰው መሆኑን። ከሱ መገናኘት ማለት በበረዶው ውሽንፍር መካከል የማለዳዋን የፀሐይ ብርሃንን እንደመመልከት ነው። የሱ ሙቀት ቅዝቃዜውን ሁሉ ያቀልጣል። ይሁን እንጂ በጊዜ ሄደት ለሱ ያላት አድናቆት ብዙም ሳይቆይ ወደ አምልኮ ተቀየረ። ምን እንደነካት የሆነውን ነገር ከማወቋ በፊት እስረኛው ሆና ራሷን አገኘች። ላደነቀችው ነገር የራሷ ስሜት ምርኮኛ ሆና ታሠረች። በሄደችበት ሁሉ ከርሱ ምስል ውጭ ምንም ነገር ማየት አልቻለችም። በሕይወቷ ውስጥም ትልቁ ፍራቻዋ እሱን ላለማስከፋት መጠንቀቅና መኖር ብቻ ሆነ። የሚሰማት ነገር ሁሉ ስለሱ ብቻ ሆነ። ያለሱ ደስታ ማለት ትርጉም የሌለው ነገር ሆነባት። እሱን መተው ማለት ነፍሷ ከአካሏ ተነጥላ የሄደች ያህል እስኪሰማት ድረስ ሆነ። የርሱ ፊት ለሷ ምግብ ነው፤ ከርሃብ የሚያስታግሳት ምግብ። ከሱ በላይ የሚቀርባትም ሆነ የምትቀርበው ምንም ነገር ጠፋ። እርሱ ለርሷ ማለት በደም ሥሯ ውስጥ እንደሚዘዋወር ደም ማለት ነው። ከርሱ ውጭ መኖር ማለት ሊታሰብ የማይችል ከባድ ነገር ሆነባት። ምክንያቱም ከርሱ ውጭ ደስታ አይታሰብምና።

በመጨረሻም ሳራ ፍቅር እንደያዛት አሰበች።

ሳራ በሕይወቷ ብዙ ነገር አሳልፋለች። ከአባቷ ጋር የተጋጨችው ገና የ16 ዓመት ወጣት ሆና ነበር። ከቤት ወጥታ ጠፋች። ከአልኮልና ከሱስ ጋር ተላምዳ ለጋ ዕድሜዋን ገፋች። በእስር ቤት የተወሰነ ጊዜ አሳልፋለች። ግና ያ ሁሉ ህመም ቢደማመር አሁን ከወደቀችበት ህመም የበለጠ አይሆንም። አሁን የራሷ ስሜትና ፍላጎት እስረኛ ነው የሆነችው።

የዚህ ዓይነቱን ነገር ነው እንግዲህ ሸይኽ ኢብኑ ተይሚያ አላህ ይዘንላቸው እንዲህ በማለት የሚገልጹት፡-

“እውነተኛ እስረኛ ማለት ልቡ ከአላህ የታሰረ ነው። እውነተኛ ምርኮኛ ማለትም ያ የስሜቱ ባርያ የሆነው ሰው ነው።” (ኢብኑ አል-ቀይም - አልዋቢል አሶዩብ፡ ገጽ 69)

ቀድሞ ከነበሩ ስቃዮቿ ሁሉ የሚከፋው ሳራ አሕመድን የማምለክ ያህል በማፍቀሯ ምክንያት የደረሰባት ስቃይ ነው። ምንም ማንም ሳያቆመው ውስጧ ዘልቆ ገባ። ይህም ሆኖ ግን ሙሉ በሙሉ ሊሞላት አልቻለም። የራሷ አድርጋው አልረካችም። ስቃዩዋም

ብርቱ ነበር። ጭው ባለ በረሃ ላይ በጥም ስቃይ እንደሚባክን ሰው ባከነች። ግና የሻተችውን ከፍተኝን ሙሉ ማድረግን አላሳካችም። ከፉኛ ተሰቃየች። የዚህ ሁሉ ስቃይ መነሻ የሆነው ፈጣሪዋን ማኖር በሚገባት ቦታ ስንኩል የሆነውን ፍጡር የሰውን ልጅ ማኖሯ ነበር።

የሳራ ታሪክ ጥልቅና ትምህርት ሊወሰድበት የሚገባ ነው። ምክንያቱም የሰውን ልጅ እውነተኛ እና ተጨባጭ ሁኔታ ሊያሳይ የሚችል ከሰተት ነውና። ሰው እንደ መሆናችን የተፈጠርነው ውስን በሆነ የተፈጥሮ ባህሪ ነው። ያም ተፈጥሮ የፈጣሪን አንድ እና ብቸኛ መሆን አስረግጠን በሕይወታችን ውስጥ በተግባር መኖር ነው። ከፈጣሪያችን እኩል ዱንያዊ ነገራትን እውስጣችን ከማስቀመጥ በላይ ምንም ነገር ማጣታችን ህመም ሊያመጣብን የሚችለው መቅሰፍት ሊያረጋግጥብን የሚችል አይደለም። ባዶነታችን ፈጣሪን ከሕይወታችን በማውጣታችን የሚመጣ መከራ ነው። ዱንያ ውስጥ በሰው ልጅ ላይ ከሚደርሱ አደጋዎች በላይ በጌታችን ላይ ማጋራትን ያህል የሰው ልጅን የሚሰብረው የለም። በአላህ ማጋራት ከባድ ወንጀል ነው። ማጋራት ሲባል ሰውን እንደ አምላክ መውደድም ሊሆን ይችላል። አላህ በቁርአኑ አፅንዖት የሰጠው የሉቅማን ምክርን ነበር።

﴿ وَإِذْ قَالَ لُقْمَٰنُ لِٱبْنِهِۦ وَهُوَ يَعِظُهُۥ يَٰبُنَيَّ لَا تُشْرِكْ بِٱللَّهِ ۖ إِنَّ ٱلشِّرْكَ لَظُلْمٌ عَظِيمٌ ﴾

«ሉቅማንም፤ ሰልጁ እርሱ የሚገስፀው ሲሆን:- ልጄ ሆይ! (ጣዖትን) አታጋራ፤ ማጋራት ታላቅ በደል ነውና፤ ያስውን ፤ (አስታውስ)።" (ሉቅማን: 13)

ሐምሌ 22 2010 'The Times of India' አንዲት የ40 ዓመት ሴት ራሷ ላይ ጋዝ በማርከፍከፍ በቤቷ ውስጥ ራስዋን አቃጥላ ያጠፋችበትን ሁኔታ ዘግቦ ነበር። ፖሊስ በወቅቱ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ ሲሰጥ፤ የሴቷ በአሰቃቂ ሁኔታ ራሷን የማጥፋት ምክንያቱ በ19 አመት የጋብቻ ሕይወቷ ውስጥ ልጅ መውለድ አለመቻሏ እንደነበር ነው።

ከዚያ ጥቂት ቀን ቀደም ብሎ ማለትም ሃምሌ 16 ቀን ፖሊስ አንድ የ22 አመት ወጣት ራሱን ማጥፋቱን ፖሊስ ገልጧል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሴት ጓደኛው ስለተወችውና ስለተለየችው ነበር ብሏል።

በነኚህ ሰዎች ላይ በደረሰው አሳዛኝ አደጋ ብዙ ሰዎች ሐዘናቸውን ገልፀዋል። ብዙዎች ልባቸው በሐዘን ተሰብሯል። ለመኖራችን ምክንያትና ዓላማ ያገኘነው ልጅ፣ አለያም በሕይወታችን ውስጥ የገባ የሆነ ሰው ከሆነ፤ የሆነ ነገር በርግጠኝነት ተሳስተናል። ይኸውም አንድ የሚያልቅ፣ ጊዜያዊ እና ሊያረጅ የሚችል ነገር የሕይወታችን መሽከርከሪያ ማዕከል፤ ለመኖራችን ምክንያት ከሆነ በእርግጥም እንሰበራለን። በኛነታችን ውስጥ

ማዕከል እንዲሆኑን ያስቀመጥናቸው ጊዜያዊ፣ አላቂና አላፊ ነገሮች ሊሆኑ አይገባም።